# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶሰት ሰዓት በ 25 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.


## ዜና ዘገባ

***መጋቢት 8 ቀን 2005 ዓ.ም.***

### ከቻይና ፍቅር የያዘው የወያኔ ቡድን የበጀት ድጎማ የሚያደርጉለትን ምእራባውያን ሀገሮች ማብጠለጠሉ አነጋጋሪ ሆነ፤

### የህወሀት ክፍፍል አለየለትም፤

### ሰማያዊ ፓርቲ በጠራው የእራት ግብዣ ላይ የተዘጋጀው ምግብ እንዲደፋ ተደረገ፤

ከቻይና ጋር እፍ ንፍስ ያለ ፍቅር የያዘው የወያኔ ቡድን ሰሞኑን በየወሩ በሚያሳትመው አዲስ ራዕይ መጽሄት በኩል ምዕራባውያንን ሲያብጠለጥል በአንጻሩ ደግሞ ቻይናን ሲያወድስ ሰንብቶዋል፡፡

ለይስሙላ የወያኔ መሪ ሆኖ የተቀመጠው የደኢህዴኑ ኃይለማርያም ደሳለኝም ሰሞኑን ከቻይናው ቲሌቪዥን ጣቢያ ጋር ባደረገው ቃለ ምልልስ ላይ በኢትዮጵያ ብሎም በአፍሪካ እየተካሄደ ያለው መሰረተ ግንባታ ቻይና ባትኖር ኖሮ እዚህ ደረጃ አንደርስም ነበር በማለት ቻይናነ ሲያወድስ ተደምጠዋል፡፡

በቅርቡ የቻይና ኮሙኒስት ብቸኛ ፓርቲ የአመራር ለውጥ አደረገ በሚል ርካሽ እና ተራ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት ሲል የወያኔ ቡድን በቃል አቀባዩ በኃይለማርያም ደሳለኝ በኩል በሰጠው መግለጫ ላይ እንዳለው ከሆነ ቻይና ባትኖር ኖሮ ኢትዮጵያ ፈጽሞ አትኖርም ነበር ብሎ በመግለጹ መላው የሀገሪቱን ሕዝቦች ያበሳጨ ከመሆኑም ባሻገር የሀገሪትዋን ዝና እና ክብር አሳንሶ ከማየት የመነጨ አባዜ መሆኑ እያነጋገረ ይገኛል፡፡

የወያኔ ቡድን ገና ወደ ስልጣን ከመጣበት ግዜ ጀምሮ የሀገሪቱን ክብር እና ዝና እያንቋሸሸ እና እያዋረደ ብሎም አንጡራ ሀብቱዋን ለባዕዳን አሳልፎ እየሰጠ የመጣ መሆኑ ቢታወቅም በአሁኑ ሰዓት የአፍሪካ ተምሳሌት ተብላ በአፍሪካ ሕዝቦች ዘንድ እንደ ትልቅ መመኪያ የምትታየውን ኢትዮጵያ የቻይና ውራጅ አስመስሎ ማቅረቡ የሚያሳፍር እና የሚያሳዝን ለሀገር እና ለህዝብ ፍቅር እና ክብር የሌላቸው እንቶ ፈንቶዎች የተናገሩት ነው ሲሉ በርካታ ምሁራኖች በብስጭት ሲናገሩ ተደምጠዋል::

የወያኔ ቡድን የቻይና ዜጎች ከሀገሪቱ ዜጎች በላይ መብታቸው ተከብሮ እንደልባቸው ተንደላቀው እንዲኖሩ ከማድረጉም ባሻገር ለኢንቨስትመንት በሚል ያለ አንዳች ግብር መሬት በነጻ እየተሰጣቸው በአንጻሩ የሀገሪቱ ባለሀብቶች ሰርተው እንዳይኖሩ ወደ ውጭ እንዲሰደዱ እያደረገ የሚገኝ ቡድን መሆኑን የተናገሩት ባለሀብት አትዮጵያውያን ዛሬ ሀገሪቱ ከቻይና ኩባንያዎች ማግኘት የሚገባትን ገቢ ሳታገኝ ይባስ ብሎ በተለያየ መልክ እየዘረፉዋት ላሉት ቻይናዎች መልሰው ማጎብደዳቸው ለሀገሪቱ ህዝቦች ያላቸውን ንቀት እና ጥላቻ ያስመሰከረ ነው ሲሉ እንባ እየተናነቃቸው የሚናገሩ ብዙ ናቸው::

ከምስራቅ እስከ ምዕራብ...... ከሰሜን እስከ ደቡብ.....ከባሌ እስከ ቦሌ...ከከተማ እስከ ገጠር ድረስ የመንገድ ግንባታ ስራ የዓለም አቀፍም ሆነ የሀገሪቱ ህግ ከሚፈቅደው ውጭ ያለ ጨረታ እየተሰጣቸው የይድረስ ይድረስ ስራ እየሰሩ በሀገር ሀብት እየቀለዱና እየተጫወቱ ላሉት ቻይናዎች ሁለመናውን አሳልፎ ሰጥቶ እያጎበደደ ዜጎች በውጭ ሀገር ያጠራቀሙትን ሀብት በሀገራችን እንስራበት በማለት ደጅ ቢጠኑም ከተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ ጋር እያያዘ ከሀገር እንዲሰደዱ እያደረገ እንደሚገኝ የጠቆሙት የችግሩ ሰለባ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ባለሀብቶች መልሶ ቻይና ባትኖር ኖሮ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር አትኖርም ነበር በማለት አሳፋሪ መግለጫ መናገሩ የኢትዮጵያን ታሪክ ጨርሶ ያጨለመ ነው ሲሉም እነዚሁ የችግሩ ሰለባ የሆኑ ባለሀብት ኢትዮጵያውያን ሲናገሩ ተደምጠዋል::

የአፍሪካ መሪዎች በጥቅም ለቻይና ተገዥ እና አጎብዳጅ በመሆናቸው በአሁኑ ወቅት 75 በመቶ የቻይና ኩባንያዎች በአፍሪካ እየተምነሸነሹ ሀብታቸውን እያፈሱ ወደ ሀገራቸው እየላኩ እንደሚገኙ ይታወቃል::

የሲሚንቶ......የቆዳ.....የመስታወት......የብረታ ብረት......የጫማ ፋብሪካ አቋቁመው በትንሽ መንቀሳቀሻ ካፒታል ስራ ጀምረው ዛሬ በዓለም ላይ ተወዳዳሪ ባለሀብት ለመሆን የበቁት የቻይና ዜጎች የወያኔ ቡድን ምቹ ሁኔታ በመፍጠሩና ልዩ ድጋፍ በማድረጉ ከመሆኑም ባሻገር አንድም ቻይናዊ ወደ ሀገር ውስጥ ገብቶ የስራ ግብርም ሆነ ሌላ ህጋዊ ክፍያ የማይከፍል ከመሆኑም ባሻገር ከሀገሪቱ ዜጎች በላይ መብቱ ተከብሮለት ያለ አንዳች ስጋት እየተንደላቀቀ የሚገኘው በወያኔ ቡድን ከፍተኛ ድጋፍ መሆኑ ይታወቃል::

ዛሬ ዜጎች በቻይና ኩባንያዎች ስራ ተቀጥረው ለመስራት አዳጋች ከመሆኑም በላይ ጥቂት የተባሉት ስራ የጀመሩ ቢኖሩም በአግባቡ በህግ በተቀመጠው መሰረት ደሞዝ የማይከፈላቸው

ከመሆኑም በተጨማሪ እሱዋም ብትሆን ግዜዋን ጠብቃ እንደማትሰጣቸውና ብዙዎቹ ዜጎች ለከፍተኛ ችግር ተጋልጠው የሚገኙበት ደረጃ ላይ መድረሱ የሚታወቅ ሲሆን በወያኔ የተወሰደ እርምጃ እንደሌለም ይታወቃል::

የወያኔ ቡድን ከቻይና ጋር በጀመረው ፍቅር የተነሳ ሌላው ቀርቶ በየዓመቱ የሚመድበውን ዓመታዊ በጀት ሳይቀር በድጎማ መልክ የሚሰጡትን ምእራባውያንን ለእድገታችን ትልቅ ማነቆዎች ናቸው በማለት ሰሞኑን አዲስ ራዕይ በተሰኘው በየወሩ በሚያሳተመው መጽሄቱ ላይ እያብጠለጠለ እና እያንቋሸሸ መሆኑ ብዙዎችን እያነጋገረ ነው::

ቻይና በሀገር እና በህዝብ ስም ብድር እና እርዳታ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ እያስታቀፈችው ያለው የወያኔ ቡድን ከምዕራባውያን ሀገሮች በተለይ ከእንግሊዝ ....ከአሜሪካ.....ከኖርዌይ.....እና ከሌሎችም የሚሰጠውን ዓመታዊ በጀት ወደ ጎን በማለት የማጣላላት ዘመቻ መጀመሩ አስገራሚ ነው ያሉት እነዚሁ ወገኖች ከቅርብ ግዜ ወዲህ በወያኔ ቡድን ውስጥ በተከሰተው ሽኩቻ የተነሳ የበላይነት ለማግኘት ሲሉ በቻይና ጀርባ ተከልለው እርስ በርስ ፉክክር መጀመራቸውንም ሳይሆን እነዳልቀረ እነዚሁ ወገኖች ግምታቸውን ይገልጻሉ::

ለዚሁ ይረዳቸው ዘንድ በቅርቡ በባህር ዳር ከተማ ይደረጋል ተብሎ ከፍተኛ ወጪ የተመደበለት የወያኔ ጠቅላላ መደበኛ 9ኛ ጉባኤ ላይ የቻይና ኮሙኒስት ፓርቲ አመራር አባላት የክብር እንግዶች እንዲሆኑ ጥሪ የተደረገላቸው መሆኑ ታውቋል::

መለስ ከሞተ በሁዋላ የስልጣን ይገባኛል ጥያቄ ያነሳው ኦህዴድ ከህወሀት ጋር ፍጥጫ በገባበት ወቅት ሳይታሰብ እና ድንገት ሕወሀት እንደገና በሁለት ቡድን ተከፍሎ እርስ በርስ ሽኩቻ መጀመሩ በወያኔ ውስጥ ምስቅልቅል ያለ ነገር መፈጠሩን ያሳየ ነው የሚሉት ለድርጅቱ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ሕወሀት እንደ 1993 ዓ.ም ግዜ እርምጃ የሚወስድ ወሳኝ ግለሰብ ባለመያዙ ያለ አንዳች እርምጃ እርስ በርስ እየተሻሸ ለረዥም ግዜ ሊቆይ እንደሚችል እየተነገረ ይገኛል::

በአሁኑ ሰዓት በባህር ዳር ሊደረግ ጥቂት ቀናት በቀረው ጉባኤ ላይ ሊሳተፉ የሚችሉትን አመራሮች አራቱም የወያኔ አባል ድርጅቶች መርጠው ስም ዝርዝር እንዲያቀርቡ አስቀድሞ መመሪያ የተላለፈላቸው ቢሆንም እስከ አሁን ሶስቱ ማለትም ኦህዴድ.. ብአዴን እና ደኢህዴን ያቀረቡ ሲሆን ህወሀት ግን ውስጣዊ ስምምነት በመጥፋቱ.........እርስ በርስ የጀመሩት ንትርክ እና ክፍፍል ባለመርገቡ ስም ዝርዝሩን ሊያቀርቡ አለመቻላቸውን እነዚሁ ቅርበት ያላቸው ወገኖች አስረድተዋል::

በሕወሀት ውስጥ የተጀመረው ክፍፍል ከግዜ ወደ ግዜ ቅርጽ እና ይዘቱን እየቀየረ አንዱን ሲሉ ሌላ እየተተካባቸው ልዩነቱ ከመጥበብ ይልቅ እየሰፋ የመጣ ሲሆን በቅርቡ ደግሞ ነባር እና ከበረሀ ጀምሮ አብረው የመጡ የቀድሞ ታጋዮች የአሁኖቹ የዞንና የወረዳ ባለስልጣናት በጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ ላይ ጥያቄ በማንሳት ሌላ ውዝግብ እየቀሰቀሱ ከፍተኛ አመራሮቹን ሰላም ነስተዋቸው እንደሚገኝ ታውቀዋል::

በህወሀት ውስጥ የተፈጠረው በሁለት ጎራ ፍልሚያ የታችኛውን አካል ያላካተተና አይመለከተውም ብለው ትተውት የነበረ ቢሆንም በእነ ስብሀት ነጋ የሚመራው ቡድን ግን

ወደ ታችኛው አመራር በመውረድ ከህወሀት ሰው ጠፍቶ ነውይ ከተማ አመጣሽ ጮሌ ስልጣኑን ሊይዝ የቻለው በማለት ቅስቀሳ በመጀመራቸው የታችኛውን አመራር ቀልብ ሊስቡ በመቻላቸው ውጥረቱ ከመቼውም ግዜ በላይ ተካርሮ እንደሚገኝም እየተነገረ ይገኛል::

በእነ ስብሀት ነጋ...ዶ/ር ደብረጽን ገብረ ሚካኤል....አርከበ እቁባይ...አዲስ ዓለም ባሌማ....ቅዱሳን ነጋ(የስብሀት እህት).....ጸጋዬ በርሄ...አባዲ ዘሙ....ኃይለ ኪሮስ ገሰሰ.....ተክለብርሀን እና ሌሎችም ያሉበት ቡድን መለስ ሕወሀትን አዳክሞ የሌሎች ድርጅት ጀሌዎች ለማድረግ የሰራው ተንኮል ነው በማለት ወደ ታችኛው አመራር በመውረዳቸው ከፍተኛ ድጋፍ እያገኙ በመምጣታቸው በህወሀት ውስጥ የተፈጠረው ልዩነት ከመቼውም ግዜ በላይ ጠንክሮ ያለ መሆኑ በስፋት እየተነገረ ነው::

አቁዋም የለውም ተብሎ ሲወገዝ እና ሲሰደብ የነበረው አባይ ጸሀዬም ለግዜው ገለልተኛ ሆኖ መስሎ ታይቶ የነበረ ቢሆንም አሁን ግን ከእነ አዜብ መስፍን ጋር ተቀላቅሎ ፍልሚያ የጀመረ ሲሆን ምንም እንኩዋን ሕወሀቶች በውስጣቸው የተፈጠረው ከባድ አደጋ ቢሆንም ምስጢራቸውን በመደበቅ ተወዳዳሪ የሌላቸው መሆኑን የሚናገሩት እነዚሁ ለድርጅቱ ቅርበት ያላቸው ወገኖች በቅርቡ በሁለት ከፍተኛ የህወሀት ሰዎች መሀከል በተነሳ ጸብ ሽጉጥ እስከ መማዘዝ ደርሰው የነበረ ቢሆንም አንድም ምስጢር ሳይሾልክ እስከ አሁን ድረስ ሊቆይ እንደቻለ ገልፀዋል::

በአባይ ወልዱ የሚመራው ቡድን አዜብ መስፍን... ሳሞራ የኑስ....ትርፉ ኪዳነ ማርያም...ሀድሽ ዘነበ....አለም ገ/ዋህድ...በየነ ምክሩ...ተክለወይኒ አሰፋ.....አባይ ፀሐዬ ከመሆናቸውም በተጨማሪ በረከት ስምኦንና አዲሱ ለገሰ ከጀርባ ድጋፍ እያደረጉ እንደሚገኝና መለስ ዘለዓለማዊ ሰው ነው ብለው የሚያምኑና በመለስ የሚያመልኩ መሆናቸውም የልዩነታቸው አንዱ ምንጭ መሆኑ ይሰማል::

በሁለቱ የህወሀት ቡድን ጭቅጭቅ እና ንትርክ ሳቢያ ግራ ተጋብተው የነበሩ ጥቂት ባለስልጣናት ችግሩን ሊያረግበው ይችላል በሚል በየአደባባዩ ተሰቅሎ የነበረው የመለስ ምስል እንዲነሳ ያደረጉ ቢሆንም ችግሩ ጨርሶ ሊወገድ ወይም ሊቀረፍ እንዳልቻለና ውዝግቡ አሁን ደግሞ መልኩን ቀይሮ ወደ ሌላ መዞሩን ነው ቅርበት ያላቸው ወገኖች የሚናገሩት::

የታችኞቹ አመራሮች በበረሀ ለ17 ዓመታት ደማችንን ያፈሰስነው.....ወንድሞቻችንን ያጣነው... አጥንታችንን የከሰከስነው...የልጅነት ወዛችንን የጨረስነው..... የከተማ ጮሌ እንዲቀመጥ ነወይ? ከህወሀት የጠቅላይ ሚኒስትርነት ቦታ መሸፈን የሚችል ጠፍቶ ነወይ? ብለው ጥያቄ እንዲያነሱ እነ ስብሀት ነጋ ውስጥ ውስጡን ቅስቀሳ በማድረጋቸው አሁን በሕወሀት ውስጥ የተነሳው ቁርቁዋሶ ይዘቱን እየለወጠ እና አቅጣጫውን እየሳተ እንዲሄድ ማድረጋቸው ተጠቁሞዋል::

ምንም እንኩዋን ውጥረቱ እየተባባሰ በመሄድ ላይ ቢሆንም በጠና ታምሞ በህክምና ላይ የሚገኘ ው ስዩም መስፍን በስካይፒ የሁለታችሁ መከፋፈል ለሌሎች ጉልበት ሊሆናቸው ስለሚችል ሁላችሁም ቆም ብላችሁ በሰከነ መንገድ ልታዩት ይገባል በማለት ምክር የለገሳቸው መሆኑን የጠቆሙት ለድርጅቱ ቅርበት ያላቸው ወገኖች እንደ ነፍስ አባት ስናየው የነበረው ስብሀት እኛን መክዳቱ ያሳዝናል የሚሉ ወገኖችም ብዙዎች መሆናቸውን ነው የሚናገሩት::

በሌላ ዜና በውስጣዊ ችግሮቹ እንደ ብራና ተወጥሮ ያለው የወያኔ ቡድን በሀገር ውስጥ የሚገኙ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ከህዝቡ ጋር የሚገናኙበትን መድረክ ሙሉ ለሙሉ እየዘጋ በመምጣቱ ተስፋ አስቆራጭ ደረጃ ላይ መድረሱን የደረሰን ጥቆማ ገለጸ፡፡

28 የተቃዋሚ ፓርቲዎች የጋራ መግባቢያ ሰነድ ለመፈራረም ፕሮግራም አዘጋጅተው አዳራሽ ለመከራየት በየሆቲሉ ለአንድ ወር ያህል ቢንከራተቱም ሳይሳካላቸው ቀርቶ በመኢአድ ቢሮ ውስጥ ሊፈራረሙ እንደቻሉ ገልጾ ሰሞኑን ደግሞ ሰማያዊ ፓርቲ የተሰኘው የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ የገንዘብ ማሰባሰቢያ የእራት ግብዣ ጥሪ አድርጎ የነበረውን ፕሮግራም በመሰረዙ ለከፍተኛ ኪሳራ መዳረጉን የፓርቲው አመራሮች በንዴት ሲገልጹ ተደምጠዋል፡፡

ቅዳሜ የካቲት 30 ቀን 2005 ዓ.ም በዋቢ ሸበሌ ሆቲል ከምሽቱ 12 ሰዓት ጀምሮ በሚደረገው የእራት ግብዣና የገንዘብ ማሰባሰብ ስራ ሊጀመር 10 ደቂቃ ሲቀረው የወያኔ ደህንነቶች ለሆቲሉ ባለቤት ማስጠንቀቂያና ማስፈራሪያ በመስጠታቸው ፕሮግራሙ እንዲሰረዝ ሲደረግ የተዘጋጀው ምግብም ከጥቅም ውጭ ሆኖ መደፋቱን የወስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ አስረድተዋል፡፡

ሰማያዊ ፓርቲ የተሰኘው አዲስ የተቃዋሚ ፓርቲ በወጣት ምሑራን የተደራጀና የተዋቀረ ፓርቲ ሲሆን ያለበትን የገንዘብ ችግር ለመቅረፍ ሲል ታላላቅ ሰዎችን እና ደጋፊዎቹን የእራት ግብዣ ጠርቶ የነበረ ቢሆንም ፕሮግራሙ ሊጀመር 10 ደቂቃ ሲቀረው ከምሽቱ 11:50 ሰዓት ላይ ድንገት የሆቲሉ ባለቤት የአጼ ኃይለስላሴ የልጅ ልጅ ልዑል በዕደማርያም በስፍራው በመገኘት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የእራት ግብዣው ተሰርዞዋል በማለት በመናገራቸው በቦታው የነበሩ እንግዶች በሀዘን ተውጠው አንዳንዶች እያለቀሱ ከምግብ አዳራሹ ሲወጡ መታየታቸውን የደረሰን ጥቆማ ገልጾዋል፡፡

የወያኔ ቡድን ለይስሙላ ከሚያደረገው የማሙያና የአካባቢ ምርጫ እራሳችንን አግልለናል ብለው አቋዋም በወሰዱት የተቃዋሚ ፓርቲዎች ላይ ጥርስ ነክሶባቸው አባሎቻቸው እና አመራሮቻቸው ላይ ከፍተኛ ክትትል እያደረገ እያዋከባቸው ሲሆን ሰሞኑንም በዋቢ ሸበሌ ሆቲል የተዘጋጀውን ከ300 በላይ ሰዎችን የሚያስተናግድ ምግብ እንዲደፋ ማድረጉ የሚያሳዝንና የሚያሳፍር ነው ሲሉ በዝግጅቱ ላይ ሊሳተፉ የተገኙት ተሳታፊዎች በብስጭት ሲናገሩ ተደምጠዋል፡፡

ቅዳሜ ዕለት ሊደረግ የነበረውን የገንዘብ ማሰባሰቢያ ዝግጅት እንዲቁዋረጥ የወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣናት በደህንነት አማካኝነት ትዕዛዝ ሰጥተው ያቋዋረጡት ሲሆን የሆቲሉ ባለቤት ልዑል በዕደማርያም ትዕዛዙን ባይቀበሉ ኖሮ በ25 ሚሊዮን ብር እዳ ክፍያ ከፍለው የወሰዱት ሆቲልን ሊነጠቁ እንደነበር የውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ አስረድተዋል፡፡